| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "ሥጉያ !" |
| ደሆሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ጥር ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2016-002 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |


# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

# ሥጉያ !

## በኢትዮጵያ ፣ በፍልስጥኤም ፡ እና ፡ በእስራኤል ።



**የተስፋ ፡ ሞት** ፡ በመሪዎች ፡ ደረጃ ፡ ሲከሠት ፥ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ይነግሥና ፥ መሪዎችን ፡ ለሰላም ፡ ወደማይሸነፍ ፡ እልክ ፡ እየመራ ፡ ንጹሓንን ፡ ጭዳ ፡ ወደማለት ፡ ጭካኔ ፡ ያደርሳቸዋል ።

ዛሬ ፡ በፍልስጥኤም ፡ በእየዕለቱ ፡ በመቶ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ንጹሓን ፡ በእስራኤል ፡ የጦር ፡ ኀይሎች ፡ የሚገደሉት ፡ የእስራኤል ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ ኀይሎች ፡ እና ፡ የሐማስ ፡ አስተዳደር ፡ ታጣቂዎች ፡ በተመጣጣኝ ፡ የኀይል ፡ ሚዛን ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ አይደለም ። አንዱ ፡ በሌላው ፡ አንጻር ፡ ተስፋ ፡ በመቍረጡ ፥ ከተስፋ ፡ መቍረጥም ፡ የተነሣ ፥ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ እንደ ፡ ጭራቅ ፡ በማየቱ ፥ "ከምድር ፡ ገጽ ፡ አጠፋዋለኹ !" ፡ ለሚያሠኘው ፡ ጭካኔው ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ድንበር ፡ አያገኝለትም ፤ ርኅራኄንም ፡ እንደ ፡ ደካማነት ፡ ይቈጥረዋል ።

ዐብረው ፡ የተገኙ ፡ ሕፃናት ፣ ሴቶች ፣ ዐዛውንት ፣ ሕመምተኞች ፡ ሳይቀሩ ፥ ከእነንብረታቸው ፡ አለምሕረት ፡ ይደመሰሳሉ ። የጦር ፡ ወንጀል ፡ ድንጋጌዎች ፡ ... ፣ ዓለም ፡ ዐቀፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ... ፥ የተ.መ.ድ. ፡ ውሳኔዎች ፡ እና ፡ ውግዘቶች ፡ ... ፣ ወዘተርፈ ፥ ከጤፍ ፡ ሳይቈጠሩ ፡ ይቀሩና ፥ በእየዕለቱ ፥ የሟቾቹ ፡ ቍጥር ፡ እያሻቀበ ፥ ሺሕ ፣ 10 ሺሕ ፣ 100 ፡ ሺሕ ፡ እያለ ፥ ጥሉ ፡ እየከረረ ፡ እና ፡ እየተስፋፋ ፡ ኼዶ ፥ በቶሎ ፡ መፍትሔ ፡ ሳይገኝለት ፡ ይቀርና ፥ ድንገት ፡ ከኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ ዐልፎ ፡ ወደ ፡ አካባቢያዊ ፡ እና ፡ ዓለም ፡ ዐቀፍ ፡ ጦርነት ፡ ይሸጋገራል ።

እዚህ ፡ ላይ ፥ **ደቡብ ፡ አፍሪቃ** ፡ በጉዳዩ ፡ ያሳየችውን ፡ አቋም ፡ በአርኣያነቱ ፡ ሳናደንቀው ፡ አናልፍም ። ከማንም ፡ የበለጠ ፡ የዐረብ ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ፍልስጥኤም ፡ እውነት ፡ ሊሟገቱ ፡ ሲገባቸው ፥ **በደልን ፡ ለብቻዋ ፡ በመቀበል ፡ ብቻ ፡ ከፍልስጥኤም ፡ የምትዘመድ ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ እስራኤልን ፡ በጦር ፡ ወንጀል ፡ በዓለም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሳለች ።** የዐረብ ፡ መንግሥታት ፡ ያሳዩት ፡ መፍረክረክ ፡ የደቡብ ፡ አፍሪቃን ፡ ፍጹም ፡ ፍትሓዊነት ፡ ይበልጡን ፡ አጕልቶ ፡ አስተጋብቶላታል ። እስራኤል ፥ በበኩሏ ፥ በክዳት ፡ የተፈጸመባትን ፡ ጥቃት ፡ ከተበቀለች ፡ ወዲያ ፥ ካሥር ፡ ዕጥፍ ፡ በላይ ፡ እስከ ፡ መበቀል ፡ መቀጠሉ ፥ ፍትሕን ፡ ከመረምረም ፥ የዓለምን ፡ ሕዝብ ፡ ስሜትም ፡ ከመናቅ ፡ ሊቈጠርባት ፡ ግዴታ ፡ ኾኗል ። ይህም ፥ ውሎ ፡ ዐድሮ ፥ ብዙ ፡ ጥቅምን ፡ እና ፡ ግምትን ፡ የሚያሳጣት ፡ መኾኑ ፡ አያጠራጥርም ። **የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ስሜት ፥ ከሰማይ ፡ በታች ፥ ከምንም ፡ ከማንም ፡ በላይ ፡ የሚፈራ ፡ እና ፡ የሚከበር ፡ ኀይል ፡ መኾኑን ፡ አለመገንዘብ ፡ በራሱ ፡ ርግማን ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ።**

**የኢትዮጵያን** ፡ ኹኔታ ፡ ለየት ፡ የሚያደርገው ፡—

- ባንድ ፡ ወገን ፥ **ምዕራባዊው ፡ ምልክዮሽ ፡ (imperialism) ፡ ለራሱ ፡ የነጠቃ ፡ ዐላማ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ የተከለብን ፡ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የተባለ ፡ የተስፋ ፡ ሞትን ፡ የሞተ ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በ"ድሮን" ፡ ጭምር ፡ የታገዘ ፡ ጦርነትን ፡ ማወጁ ፥ ይህም ፡ ጭፍጨፋ ፡ በዓለም ፡ ማወራኛዎች ፡ ታፍኖ ፡ አለመሰማቱ** ፡ ሲኾን ፥
- በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ የተገፈፈውን ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

**ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ ለማስመለስ ፡ እና ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ለማደር ፥ በተስፋ ፡ ሕይወት ፡ የተመላው ፥ ባልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፡ በፋኖ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዐርበኝነት ፡ እየተመራ ፡ የሚታገለው ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።**

በኢትዮጵያም ፡ በፍልስጥኤምም ፡ የሚካኼዱት ፡ ጦርነቶች ፡ የንጹሓንን ፡ ደም ፡ በገፍ ፡ በማፍሰሳቸው ፡ እኩል ፡ ምድሪቱን ፡ ያረክሳሉ ። ደም ፡ ደምን ፡ ይጠራልና ፥ ዛሬ ፡ ከሰላም ፡ ዓለም ፡ ኾነው ፡ የሚመለከቱ ፥ ዐልፎም ፡ መጠፋፊያ ፡ መሣሪያን ፡ የሚሼጡ ፡ እና ፡ የሚያቀብሉ ፡ ኀይሎች ፥ ነገ ፡ ወደጦርነት ፡ ዓለም ፡ ድንገት ፡ ተሽቀንጥረው ፡ እንደሚጣሉ ፡ ይወቁ ፥ ይረዱ ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ እናብር!**

ኢ ሀ ሥ አ

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

**ሥልጡንሕዝብና ።**
**www.slttunhzb.net**


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።